www.abyssinialaw.com



14ኛ ዓመት ቁጥር 5
14th Year No 5

ባህር ዳር ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም
Bahir Dar 18th, December 2009

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 12.10 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box |



## ማውጫ

**ደንብ ቁጥር 63/2001 ዓ.ም**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## CONTENTS

**Regulation No. 63/2009**

The Amhara National Regional State The Design and Supervision Works Enterprise Establishment and Powers and Duties Determination, Council of Regional Government Regulation.

## ደንብ ቁጥር 63/2001 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቱን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO. 63/2009

A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT AND DETERMINATION OF POWERS AND DUTIES OF THE DESIGN AND SUPERVISION WORKS ENTERPRISE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



ክልሉ ሰፊ የውሃ ሃብትና በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ባለቤት በመሆኑ፣ የክልሉን ግብርና ደረጃ በደረጃ ከዝናብ ጥገኝነት በማውጣት በመስኖ ልማት ዓመቱን ሙሉ የማልማትና የመሬት አጠቃቀምና የጉልበት አጠቃቀምን በማጐልበት ምርታማነትንና የሥራ እድልን በማስፋፋት ለክልሉና ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ገንቢ አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚያስችል በመታመኑ፣

WHEREAS, it is believed to make a very positive contribution to the economic growth of the region as well as the country by boosting productivity and promoting job-opportunity and enhancing land use and labour management and thereby cultivating the land year-round using irrigation because the region is endowed with vast water resource and with the land capable of being developed by irrigation so as to, step by step, extricate agriculture of the region from rain dependent;

የዝናብ አስተማማኝነት አለመኖርና ከመሬት ምርታማነት መቀነስ ጋር በተያያዘ በክልሉ እየታየ ያለውን የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር የመስኖ ልማትን በማስፋፋት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ በሂደቱ የግብርና እድገት ውጤት የሆነውን ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት ግብ የሚያሳካ ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ የክልሉን ንፁህ የመጠጥ ውሃ ፍላጐት ማሟላት የወቅቱ ጥያቄ በመሆኑና በክልሉ ሰፊ የመንገድና ህንፃ ግንባታ ሥራዎች ፍላጐት ያለ በመሆኑ፣

WHEREAS, to promote agricultural produce and its productivity and to materialize food security which is now the problem and evident in the Region due to rain-deficit and reduction of land productivity through extending irrigation development has been necessary to support for achieving goals of export-led industrial development which is the outcome of agricultural development and to satisfy a need of potable water of the region is a current issue as well as there has also been needs of vast works of road and building construction in the region;

የተጠቀሱትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በክልሉ ውስጥ የውሃ፣ የመንገድና ሕንጻ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ተግባራትን በጥራት ማካሄድና ራሱን የቻለ ጠንካራ መንግስታዊ የልማት ድርጅት ማቋቋም ተገቢ በመሆኑ፣ በቂና የሰለጠነ ባለሞያ ኑሮ አቅሙን በማደራጀት ክልሉ የሚጠቀምበትን አሠራር መፍጠር በማስፈለጉ፣

WHEREAS, in order to attain the aforementioned objectives, it has been appropriate to establish an autonomous government development enterprise and efficiently carry out design and supervision activities of water, road and building works in the region as well as to create working procedure through which the region may use, having existed sufficient and trained professional by organizing its capacity thereof.

www.abyssinialaw.com



የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of Amhara National Regional State, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58, sub. Art.2 and 7 of the Revised Regional Constitution, hereby issues this regulation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "አማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 63/2001 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል"

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

1. "ድርጅት" ማለት በዚህ ደንብ የተቋቋመውን አማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት ነው።
2. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሠረት የተቋቋመ አማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው።

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amhara Design and Supervision Works Enterprise Establishment and Powers and Duties Determination Regulation No. 63/2001."

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. "Enterprise" shall mean the Amhara Design and Supervision Works Enterprise established under this regulation.
2. "Board" shall mean the Managing Board of Amhara Design and Supervision Works Enterprise established pursuant to Art. 8 of this regulation hereof. "

www.abyssinialaw.com



# ክፍል ሁለት

# ስለድርጅቱ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አደረጃጀትና ዓላማዎች

## 3. ስለ ድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት

1. አማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት /ከዚህ በኋላ ድርጅቱ እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድርና እሱ ለሚሰይመው የሥራ አመራር ቦርድ ይሆናል።

## 4. ስለ ድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት

1. የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ባህር ዳር ከተማ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍና የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ።

# PART TWO

# ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY, ORGANIZATION AND OBJECTIVES OF THE ENTERPRISE

## 3. Establishment and accountability of the Enterprise

1. The Amhara Design and Supervision Works Enterprise /hereinafter referred to as “The Enterprise”/ is hereby established as autonomous enterprise having legal personality under this regulation.
2. The Enterprise shall be established for unlimited period of time and be accountable to the president of the Amhara National Regional Government and to the management board designated by same.

## 4. Head Office of the Enterprise

1. Head office of the enterprise shall be in Bahir Dar.
2. Without prejudice to sub. Art. 1 of this Art. hereof, the enterprise may, as may be necessary, have branch and project offices to be established in any other places.

www.abyssinialaw.com



## 5. ድርጅታዊ አቋም

ድርጅቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ም/ዋና ሥራ አስኪያጆች ይኖሩታል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
3. ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈልጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፣ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
4. የሠራተኞች ቅጥርና የክፍያ ሁኔታን አስመልክቶ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 6. የድርጅቱ ዓላማዎች

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ የእርሻ መሬት የመስኖ ውሃ አቅርቦት እንዲያገኝ ጥራት ያለው ጥናት ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች በቅልጥፍና ማከናወን፣
2. የክልሉን ሕዝብ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ የመጠጥ ውሃ ሥራዎችን ጥናት፣ ዲዛይን እንዲሁም የቁጥጥር ሥራ ጥራት ባለው መረጃ ማከናወን፣
3. የመንገድ፣ የሕንፃና ኃይድሮፓወር ጥናት ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር አገልግሎት በመስጠት የክልሉን የመሠረተ ልማት ችግሮች መፍታት፣

## 5. Organizational Structure

The enterprise shall have the following bodies:-

1. a Managing board;
2. a chief manager and deputy chief mangers to be appointed by the head of the Regional Government. Particulars shall be determined by a directive.
3. Other heads and employees necessary at each level of the structure. Particulars shall be determined by a directive.
4. With regard to conditions of recruitment and payment of employees shall be determined by a directive.

## 6. Objectives of the Enterprise

The Enterprise shall have the following objectives:

1. to efficiently carry out quality study, design and supervision works in such a way that farm land of the region may obtain supply of irrigation water;
2. with reliable information, to carry out study, design and supervision activities of drinking water so as to make the regional people beneficiary of potable water;
3. to resolve problems of infrastructure of the region by providing service of study and design of road, building and hydropower and supervision of construction thereof;

www.abyssinialaw.com



4. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ የጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ተግባራትን ማከናወን።

## ክልፍ ሦስት

## የድርጅቱ ሥልጣን፣ ተግባር እና ድርጅታዊ አቋም

### 7. የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የመስኖና ድሬኔጅ፣ የከርሰ ምድር፣ የገፀ ምድርና የዝናብ ውሃ ተጻምረው የአካባቢውን የውሃ ሃብት ጥቅም ላይ የሚያውል የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ይሠራል። ጥናቱንና ዲዛይኑን ለአሰሪው መ/ቤት ያስረክባል። ግንባታው ሲካሄድ ይቆጣጠራል።
2. በጐርፍ ውሃ፣ በመሬት መሸርሸር ምክንያት የወንዞችና ተፋሰሶች አቅጣጫ መሳትና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች፣ የከተሞችን ልማት እንዳያጠፋና እንዳያደናቅፍ የወንዞችን ተፈጥሯዊ መፍሰሻና የጐርፍ መቀልበሻ አማራጮችን ያጠናል። ዲዛይን ይሠራል። ለአሰሪው መ/ቤት ያስረክባል። የግንባታውን ሂደት ይቆጣጠራል።

4. to carry out such other similar activities of study, design and supervision as deemed necessary.

## PART THREE

## POWERS AND DUTIES AND ORGANIZATIONAL STRUCTURE OF THE ENTERPRISE

### 7. Powers and duties of the Enterprise

The enterprise shall have the following powers and duties:

1. Perform activities of study and design that enable water resource of the surroundings on use, having been combined irrigation and drainage, ground, surface and rain water. Submit the study and design to the office operating its construction. Supervise over while the construction is carried out.
2. Study possibilities of natural flow /course/ of rivers and flood diversion in order not to devastate and obstruct farm and grazing lands and development of cities on account of deflection of direction of rivers and drainages due to flood and land-slide. Design and submit same to the office which operates its construction. Supervise over operation of the construction.

www.abyssinialaw.com



3. ከመስኖና ድሬኔጅ እና ከመጠጥ ውሃ ጋር የተያያዙ የሃይድሮሎጂ፣ የሃይድሮጂኦሎጂ የሜትሮሎጂና ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችና ጥናቶችን ከአካባቢው፣ ከክልሉ፣ ከአገር አቀፍና ከአለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር ያገናዘበ መረጃ ይሰበስባል። ለጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራው ጥቅም ላይ ያውላል።
4. የተፋሰስ ልማት፣ የግድብም ሆነ የወንዝ ጠለፋ ሥራ እንዲሁም የመስኖ አውታር ሥራ የአካባቢው ማህበራዊና ኢኮኖሚያው የአግሮኖሚ ሁኔታ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ተጓዳኝ ጥናቶች ያካሂዳል። ዲዛይን ይሠራል። በግንባታ ሂደት የቁጥጥር ሥራ ይሠራል።
5. የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አማራጮችን የገፀ-ምድር፣ የከርሰ ምድርና የዝናብ ውሃ ከመለየት ጀምሮ ዙሪያ መለስ ጥናት ያደርጋል። በጥናቱ መሠረት ልዩ ልዩ የዲዛይን ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ዲዛይን ይሠራል። ለአሰሪው መ/ቤት ያስረክባል። ግንባታው በሚካሄድበት ወቅት የግንባታውን ጥራት የሚመለከት ቁጥጥር ያደርጋል።
6. የመንገድ፣ የህንፃና የሃይድሮፓወር ዲዛይን ሥራ ይሠራል። የግንባታ ቁጥጥር ያደርጋል።

3. Collect information, in harmony with the surrounding, regional, national and international circumstances of hydrology, hydro-geology, metrology and other related information and studies that are related to irrigation and drainage and drinking water. Put same to good use in the activity of study, design and supervision thereof.
4. Carry out activities of basin development, dam and river diversion as well as irrigation sector work, conditions of socio-economic agronomy, evaluation of environmental impact and other connected studies. Make design and supervise over during its construction.
5. Conduct all-round study of possibilities and options of provision of drinking water including identification of surface, ground and rain water; make a design by employing various technology of design in accordance with the study. Submit same to the office which operates its construction. Supervise over quality of the construction at the time of its operation.
6. Make design work of road, building and hydropower. Undertake supervision of construction.

www.abyssinialaw.com



7. የተቋሙን የሰው ሃይል አቅም ከመስኖና ድሬኔጅ፣ ከመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን፣ ከመንገድና የህንፃ ግንባታ እንዲሁም የሃይድሮፓወር ሥራዎች የጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ብቃት ከማጐልበት አኳያ የተለያዩ የምህንድስና የሐይድሮሎጂ፣ የስትራክቸር፣ የሜትሮሎጂ፣ የሃይድሮጂኦሎጂ፣ የቅየሳ፣ የንድፍ፣ የአፈር ምርምር፣ የአግሮኖሚ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ አጫጭር ሥልጠና ይሰጣል። ከልዩ ልዩ የጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ቴክኖሎጂ ጋር ያስተዋውቃል። የተገኘው እውቀት በተግባር እንዲተረጐም ይሠራል። በቀጣይነት እጥረቶችን እየፈተሸ የአቅም ግንባታ ያካሂዳል።

8. ለጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ የሚያገለግሉ አሠራሮችን ይቀይሳል። የቅየሳ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች፣ የዲዛይን ቴክኖሎጂዎች (Soft Wares)፣የአፈርና የሌሎች ምርምር ውስጠ ድርጅት፣ ከጥናትና ዲዛይን ጋር የተያያዘ የኮምፒዩተር እውቀትና ቴክኖሎጂ ማዕከል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የሃይድሮሎጂ ቴክኒካል ምርመራዎች የሚሆኑ መሳሪያዎችን ያሟላል። በዚህ ዙሪያ የሚገኙ አገር አቀፍና አለማቀፍ ልምድ ያጠናል። ጠቃሚ የተባሉትን ተግባራዊ

7. Provide short training in various engineering, hydrology, structure, meteorology, hydro-geology, surveying, design, soil research, agronomy, social and economy as well as other related issues with regard to promoting efficiency of human resource capacity of the institution in irrigation and drainage, drinking water and sanitation, road and building construction as well as hydropower works, study, design and supervision thereof. Familiarize them with various technologies of study, design and supervision. Work so as to be practiced the acquired knowledge. Having identifies limitations; carry out capacity building in a sustainable manner.

8. Devise working-systems to be used for the work of study, design and supervision. Organize and direct surveying materials and technologies, designing technologies (Soft ware), internal organization of soil and other researches, center of computer knowledge and technology. Fulfill materials to be used for hydrology technical examination. Study national and international experiences found in this area and thereby implement those which are said to be useful thereof.

www.abyssinialaw.com



ያደርጋል።

9. የጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ወጭዎችን ለመወሰንና የድርጅቱን የአትራፊነት ወሰን ለማወቅ የጥናት ጊዜና የሚፈልጋቸውን የባለሙያና የቁሳቁስ ቅንብር ያጠናል። ይወስናል። ለቁጥጥር የሚያስፈልጉ የሰው ሃይል፣ የቴክኖሎጂና የቁሳቁስ ቅንብር ያጠናል፤ የጥናትና ዲዛይን እንዲሁም የግንባታ ቁጥጥር ዋጋ ይወስናል።

10. ከመሠረተ ልማት ሥራዎች አኳያ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ድርሻ ካላቸው አካላት ጋር በጋራ ይሠራል። ዋነኛ ደንበኞቹ የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ፣ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና የመስኖና ድሬኔጅ የሥራ ሂደት /መምሪያ/፣ የገጠር መንገድና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ቀጥተኛ የሆነና በመግባባት ላይ የተመሠረተ የሥራ ስምሪት ያደርጋል። ከሌሎች አገር በቀልም ሆኑ በውጭ ያሉ ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሠራል። ልምድ ይለዋወጣል።

11. የድርጅቱ የገቢ ምንጭ

ሀ/ ድርጅቱ ከሚያገኘው ትርፍ፣

ለ/ ድርጅቱን ለመደገፍ ፍላጎት ካላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ

9. Study and determine the study-time and arrangement of professionals and utensils it requires so as to know limit of profitability of the enterprise and to determine expenditures of study, design and supervision. Study human resource, arrangement of technology and utensils necessary for supervision. Determine price of study and design as well as supervision of construction.

10. Work in conjunction with stakeholders having direct and indirect involvement thereof. Taking account of that its chief clients are Water Resource Development Bureau, Water Works Construction Enterprise and Irrigation Drainage Process /Department/, Rural Road Authority and other pertinent institutions, undertake work engagement on the basis of direct and mutual understanding. Work in conjunction with other local and /or oversea enterprises. And share experience with other enterprises.

11. Source of Income of the Enterprise shall be:

A. The profit it shall make;

B. It shall be form government and non-government enterprises having an interest to

www.abyssinialaw.com



ድርጅቶች ይሆናል።

12. ድርጅቱ የራሱ አርማና ማህተም ይኖረዋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

13. ድርጅቱ የንብረት ባለቤት ይሆናል። ቦንድ ይገዛል፣ ይሸጣል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

14. ሌሎች የድርጅቱን ዓላማዎች ያሳካሉ ተብለው የሚታሰቡ ተግባራትን ያከናውናል።

## ክፍል አራት

## የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት፣ ተጠሪነትና፣ ሥልጣንና ተግባር

### 8. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አደረጃጀትና የሥራ ዘመን

ሀ/ የሥራ አመራር ቦርዱ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል፣

ለ/ የቦርዱ አባላት በክልሉ ር/መስተዳድር ይሰየማሉ፣

ሐ/ ቦርዱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል፣ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የቦርድ ፀሐፊና አባል ይሆናል፣

መ/ የቦርድ እና የአባላቱ የሥራ ዘመን በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይወሰናል፣

support the enterprise.

12. The enterprise shall have its own emblem and seal. Its particulars shall be determined by a directive.

13. The enterprise shall own property, buy and sell bond, as well as sue and be sued in its name.

14. carry out such other activities to be assumed to attain objectives of the enterprise.

## PART FOUR

## ORGANIZATION, ACCOUNTABILITY AND POWERS AND DUTIES OF A MANAGING BOARDOF THE ENTERPEISE

### 8. Organization and Term of Office of the Managing Board Members

A. The managing board shall have members numbering form five through nine;

B. Members of the board shall be designated by the head of the Regional Government;

C. The board shall have its own chair-person and secretary. The manager of the enterprise shall be secretary and member of the board;

D. Term of office of the board and its members shall be determined by the Council of the Regional Government;

www.abyssinialaw.com



ሠ/ የቦርዱ አባላት ጥቅማ ጥቅም በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ሊወሰን ይችላል፣

ረ/ የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

## 9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ ድርጅቱ የሚመራበትን አጠቃላይ ፖሊሲ በማመንጨት ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል። በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል።

ለ/ ድርጅቱ የሚመራባቸውን ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል።

ሐ/ የድርጅቱን ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅና ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች ሌሎች የሥራ ሂደት መሪዎች በሚወጣው የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት ለክልሉ ር/መስተዳድር አቅርቦ ያሾማል።

መ/ ድርጅቱ በሰው ሃይል፣ በመሳሪያና በሥራ አመራር የሚጠናከርበትን መንገድ ያስጠናል፣ ጥናቱንም ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

ሠ/ የድርጅቱን ንብረት በአግባቡ መያዙን፣ የገንዘብና የሰው ሃይል አጠቃቀሙም

E. Benefits of the board members may be determined by the council of the Regional Government, as may be necessary.

F. The board shall be accountable to the head of the Regional Government.

## 9. Powers and Duties of the Board

The board shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

A. Initiate general policy through which the enterprise may be directed, submit same to the council of the Regional Government and cause to be approved. Follow up its implementation.

B. Issue various rules and directives by which the enterprise to be managed.

C. Approve plan and budget of the enterprise and follow up its implementation. Submit to the head of the Regional Government and have to be appointed manager and deputy managers and other process owners of the enterprise pursuant to the implementation guideline to be issued in the future.

D. Cause the study of a way through which the enterprise to be strengthened in human resource, material and management as well as cause its implementation whenever it finds the study useful.

E. Ensure that the property of the enterprise is properly handled, utilization of its finance and human resource is efficient to execute

www.abyssinialaw.com



የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዓላማዎች እንዲሁም የድርጅቱን አላማ ለማስፈፀም ብቁ መሆኑን ያረጋግጣል፣

ረ/ የቦርዱን ውስጠ ደንብና ሥነ-ሥርዓት ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሰ/ ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤትና ርዕሰ መስተዳድሩ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል።

socio-economic objectives of the Region as well as that of the enterprise.

F. Formulate internal guidelines and procedure of the board and implement same.

G. Submit to the Council and Head of the Regional Government timely reports concerning the activities of the enterprise.

## 10. የቦርዱ የስብሰባ ሥርዓት

ሀ/ ቦርዱ በ3 ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣

ለ/ ከቦርዱ አባላት አብላጫው በስብሰባው ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል፣

ሐ/ የቦርድ ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

መ/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብስባ ሥነ-ሥርዓትና ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## 10. Meeting Procedure of the Board

A. The board shall convene its regular meeting once in three months. It may, however, hold extra ordinary meeting at any time where it finds it necessary.

B. There shall be a quorum where majority of members of the board are presented at its meeting.

C. Decision of the board shall be passed by majority vote. In case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote.

D. Without prejudice to the provisions of this Art, the Board may issue its own meeting procedure and guideline.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አምስት

## ስለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

### 11. የዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በር/መስተዳድሩ የሚሰየም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ የድርጅቱን የሥራ መዋቅር፣የሠራተኞችን ደመወዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
3. የድርጅቱን ሂሣብ ለማንቀሳቀስ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣
4. የድርጅቱን የአጭር የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ ፕሮግራም እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ ያውላል፣
5. ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጁ የሆኑ የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባና

## PART FIVE

## POWERS AND DUTIES OF THE MANAGER OF THE ENTERPRISE

### 11. Powers and Duties of the chief Manager

Having been designated by the Head of the Regional Government, the chief manager of the enterprise shall have the following powers and duties:

1. Manage, administer and supervise over the activities of the enterprise;
2. Organize office of the enterprise, prepare and submit to the board job structure salary and allowance of the employees of the enterprise and follow up its implementation up on approval;
3. Open bank account so as to operate account of the enterprise;
4. Prepare and submit to the board short, medium and long term plan budget and working program of the enterprise and put into place up on approval.
5. Submit to the board recruitment, assignment and dismissal of working heads accountable to the chief manager and

www.abyssinialaw.com



ስንብት በሚመለከት ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል፣

6. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባለው ሕግና በድርጅቱ የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፣

7. ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፣

8. የቦርዱን ውሣኔ ይፈፅማል፣ ያስፈጽማል፣

9. ድርጅቱ ከሚሰጠው አገልግሎት የሚገኘው ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፣

10. ድርጅቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነትና ውለታ ሁሉ መ/ቤቱን ይወክላል፣

11. ለክልሉ ር/መስተዳድርና ለሥራ አመራር ቦርድ የየሩብ ዓመትና ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም እና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣

12. በቦርዱ የሚሰጡትንና ለድርጅቱ ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች ተግባራት ያከናዋናል፣

13. ስለ ም/ዋና ሥራ አስኪያጆች ሥልጣንና ተግባር፡-

 1. በዋና ሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ፣
 2. ዋና ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ

thereby have same approved.

6. Without prejudice to sub. Art. of this Art. Hereof, recruit, administer, promote and dismiss employees, pursuant to pertinent law and administrative rules of the enterprise,

7. cause the withdrawal of money in accordance with budget and working program appropriated to the enterprise and thereby supervise over its implementation as well;

8. Implement and cause its implementation decision of the board;

9. Supervise over that the income obtained form the service which the enterprise provides thereof is properly collected.

10. Represent the enterprise in all its relation and contract with third parties;

11. Prepare and submit quarterly performance and account report to the Head of the Regional Government and Managing Board.

12. Perform such other duties useful to the enterprise as may be given to him by the board.

13. Powers and Duties of the Deputy Chief Mangers

 1. Perform duties as are specifically given to them by the chief manager;
 2. one to be delegated by the chief manager, act on behalf of the chief

www.abyssinialaw.com



በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚወከለው ተተክቶ ይሠራል።

manager in his absence or under the circumstances where he is unable to perform his normal duties.

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 12. ስለ ድርጅቱ የመነሻ ካፒታልና የበጀት ዓመት

ሀ/ የድርጅቱ የመነሻ ካፒታል

ለድርጅቱ የመነሻ ካፒታል ብር መቶ ሚሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 25 ሚሊዮን በጥሬ ገንዘብ እና 40 ሚሊዮን በዓይነት ተከፍሏል።

ለ/ የድርጅቱ የበጀት ዓመት ከመንግስት የበጀት ዓመት ጋር አንድ ይሆናል።

### 12. Initial Capital and the Budget Year of the Enterprise

A. Initial capital of the Enterprise

The initial capital of the enterprise is one hundred million. Twenty five million is disbursed in cash and forty million is in kind.

B. The budget year of the Regional State shall be the budget year of the enterprise.

### 13. የሂሣብ መዛግብት

1. ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግቶች ይይዛል፣
2. የድርጅቱን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝ በተመለከተ በቦርዱ ተቀባይነት ያላቸው የሂሣብ አሠራሮች ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወጣል።

### 13. Books of Account

1. The enterprise shall keep complete and accurate books of account
2. With regard to keeping books of account and financial related documents, the board may cause acceptable account operation to be pup into place. Particulars shall

### 14. የሂሣብ ምርመራ

የድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጪ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

### 14. Auditing

The books of account and financial related documents of the enterprise shall be audited by the office of the Auditor General of the Regional State or external Auditors to be assigned by the Board.

### 15. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ታይቶና ተመርምሮ ከፀደቀበት ከታህሳስ 24/2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

### 15. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of January 2, 2009.

www.abyssinialaw.com



ባህር ዳር
ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

Done at Bahir Dar
This 2nd day of January, 2009
Ayalew Gobezie
Head of Government of the Amhara
National Regional State